# የአባሰንጋ በሽታ መከላከያ መንገዶች

እንሰሳትን ማስከተብ

የታመሙ የሚመስሉ ወይም የሞቱ እንሰሳትን አለመንካት፤ መንካት ግድ ከሆነም እጅን በጓንት ወይም በላስቲክ መሸፈን እና ወዲያውኑ እጅን በንጹህ ውሃ እና ሳሙና በደንብ መታጠብ

በአባሰንጋ በሽታ የሞቱ እንሰሳትን ከእንሰሳት ህክምና ወይም ከጤና ባለሙያ ጋር በመሆን በጥንቃቄ ማቃጠል ወይም መቅበር

ከሞቱት እንስሳት ጋር የተነካኩ ቁሳቁሶች የእጅ ጓንት ፤ ላስቲክ ፤ ቢላ እና የመሳሰሉትን ከሞተው እንሰሳት ጋር ቃጠል ወይም መቅበር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
Federal Democratic Republic of Ethiopia

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

JOHNS HOPKINS
Center for Communication Programs



# አባ ሰንጋ
## ከእንስሳት ወደ ሰው ይተላለፋል

## የአባሰንጋ በሽታ ምንድን ነው?

የአባሰንጋ ወይም ቁርባ በሽታ ከእንሰሳት ወደ ሰው የሚተላለፍ አደገኛ በሽታ ነው። የአባሰንጋ በሽታ ህክምና ካልተደረገ በአጭር ጊዜ ለሞት ይዳርጋል።

በሽታው በዋነኛነት በፍየሎች፣ በጎች፣ ላም እና በሬዎች፣ ፈረሶች እና ሌሎች የግጦሽ እንሰሳት ላይ ይታያል።

ጥሬ/ያልበሰለ ስጋ እና ሌሎች የእንሰሳት ውጤቶች መመገብ ወይም የታመሙ እንስሳትን ቆዳ፣ ጸጉር፣ አጥንት እና ሌሎች የእንስሳት ፈሳሾች በመንካት በሽታው ይተላለፋል።

## የአባሰንጋ በሽታ ምልክቶች



### የቆዳ ላይ ምልክቶች

የነፍሳት ንክሻ የሚመስል ትንሽ የቆዳ ቁስል ፤ ቡናማ ቀለም ያለው ጠንከር ያለ እብጠት እና በዙሪያው ውሃ የቋጠሩ ቁስሎች



### የመተንፈሻ አካላት ላይ የሚታዩ ምልክቶች

ትኩሳት ፤ ብርድ ብርድ ማለት ፤ ማላብ ፤ የትንፋሽ መቆራረጥ ፤ የልብ ምት ፍጥነት መጨመር እና ደረቅ ሳል

### የጨጓራ እና የአንጀት ምልክቶች

የሆድ ህመም ፤ ማቅለሽለሽ እና ትውከት

**ከእነዚህ ምልክቶች አንዱን እንኳን ካዩ በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም ይሂዱ።**